# በውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር
# የመስኖ ልማት ዘርፍ

## የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ
## (2013-2022)

ታህሳስ 2012

# ይዘት


ማጠቃለያ ........ iii

1. መግቢያ ........ 1

1.1 መነሻ ........ 1

1.2 የመሪ ዕቅዱ አስፈላጊነት ........ 2

1.3 ዓላማ ........ 2

2. የመስኖ ዘርፍ ትንተና ........ 3

2.1 ዘርፉ አሁን ያለበት ደረጃ ........ 3

2.2 ለዘርፉ ልማት ወሳኝ የሆኑ ሰብአዊና ቁሳዊ ሃብቶች ........ 4

2.3 የ SWOT እና PESTLE ትንተና ........ 6

3. የባለድርሻ አካላት ትንተና ........ 10

4. የመስኖ ልማት ዘርፍ የስራ ድርሻና የሌሎች አገሮች ተሞክሮ ትንተና ........ 22

4.1 በዘርፉ የሚሰሩ ስራዎች ........ 22

4.2 የመስኖ ልማት ዘርፍ የስራ ማዕቀፍና ተጓዳኝ ፖሊሲዎች ........ 22

4.3 የመስኖ ልማት ዘርፍ ዋና ተዋናዮች ........ 24

4.4 በመስኖ ልማት የአገራት ልምድና ተሞክሮ ........ 25

4.5 በዘርፉ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ........ 27

5. የትኩረት አቅጣጫ ........ 29

5.1 ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች ........ 29

5.2 ስትራቴጅክ ምሰሶዎች፣ ግቦችና ቁልፍ ተግባራት ........ 30

6. የተግባር ዕቅድ ........ 40

7. የፋይናንስ ፍላጎት ........ 44

8. ክትትልና ግምገማ ........ 47

9. ዕቅዱን ለማስፈፀም ታሳቢ የተደረጉ ነገሮችና ስጋቶች ........ 54

## ማጠቃለያ

በአብዛኛው ዝናብ ተኮር የሆነው የአገራችን ግብርና በተለያዩ ጊዜ በሚያጋጥም የዝናብ እጥረት እና ስርጭት መዛባት ምክንያት የሚጠበቀውን ምርትና ምርታማነት ማስገኘት አልቻለም፡፡ ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የግብርናውን ዘርፍ ማዘመንና የመስኖ ልማትን ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት ዘርፉ በመንግስት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ሰፊ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም አገሪቷ ካላት የውሃና የመሬት የማልማት አቅም አንፃር ግን እስከአሁን የመስኖ ልማቱን የማስፋፋት ስራው እና ፍጥነቱ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም እንደምክንያት ከሚቀርቡ ዋና ዋና ችግሮች መካከል ደካማና ያልተረጋጋ ተቋማዊ የመስኖ አመራርና አደረጃጀት፤ በመስኩ ብቃት ያለው የሰው ሀይል እጥረት፣ የፋይናንስ አቅርቦት ዕጥረት፣ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፣ ውስን የቴክኖሎጂ አቅም እና የገበያ ትስስር አለመኖር ይገኙበታል፡፡ የውሃ ሃብት መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር በመስኖ ልማት ዘርፍ የሚታዩትን እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ የተሻለ አፈጻጸም ማስመዝገብ እንዲቻል ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ ይህንኑ የመስኖ የማልማት ሥራን በአገሪቱ በላቀ ሁኔታ መምራት ይቻል ዘንድ ይህ የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ተነድፏል፡፡ ይህ ዕቅድ አሁን ዘርፉ ያለበትን ሁኔታ፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን፤ መልካም አጋጣሚዎችና ዘርፉን ሊጋጥሙት የሚችሉ ስጋቶች እንዲሁም ዘርፉ ከባለድርሻ አካላት ጋር ሊኖረው የሚገባውን ግንኙነት በዝርዝር በመፈተሽ፤ ከዚያም አልፎ የሌሎች አገራትን ተሞክሮና ልምድ ግምት ውስጥ በማስገባት ለዘርፉ እድገት ትኩረት የሚሹ አምስት የስትራቴጂክ ምሰሶዎችን በመለየት ተዘጋጅቷል፡፡ እነዚህም በመስኖ ልማት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤ የስራ ዕድል መፍጠር፤ የመንግስት ወጭ ቅነሳና እና አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማጎልበት፤ተቋማዊ አቅምና የዘርፉን የሰው ሃብት ልማት ማሳደግ እና የስርዓተ-ፆታና አካል ጉዳተኞች አካታችነት ማረጋገጥ ሲሆኑ ለእያንዳንዱም ግቦችና ቁልፍ ተግባራት ተቀምጠላቸዋል፡፡ በተጨማሪም ለእቅዱ መሳካት ዝርዝር የአፈፃፀም ስልትና የበጀት ፍላጎትን የያዘ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን እቅዱ በቁርጠኝነት እንዲመራም የክትትልና ግምገማ ስርዓት ተካትቶበት ቀርቧል፡፡

# 1. መግቢያ

## 1.1 መነሻ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተመሰረተው በአብዛኛው በግብርናው ዘርፍ ላይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ይህ ዘርፍ በዝናብ ጥገኝነት ላይ የተመረኮዘ የአመራረት ዘዴ የሚከተል በመሆኑ በተለያዩ ጊዜ በሚያጋጥም የዝናብ ስርጭት መዛባት እና እጥረት ምክንያት አገሪቷ በተደጋጋሚ ለድርቅና ርሃብ እየተጋለጠች ትገኛለች፡፡ ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የግብርናውን ዘርፍ ማዘመንና የመስኖ ልማትን ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡ ከተፈጥሮ ሃብት አኳያ አገሪቱ ለዚሁ ተግባር ሊውል የሚችል በቂ የውሃ ሃብትና ሰፊ መሬት አላት፡፡

የመስኖ ልማት የዝናብ እጥረት ተፅዕኖን በመቀነስ እንዲሁም በዓመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ ማምረትን በማስቻል የግብርናን ምርታማነት ለማሳደግ ያስችላል፡፡ እንዲሁም የመስኖን ልማት ማስፋፋት የምግብ ሰብልን በበቂ መጠን በማምረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ለመጣው ህዝብ የምግብ ሰብል ፍላጎት ማርካት ባለፈ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ግብአት በማቅረብ የአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ላይ ቁልፍ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

በአገራችን ዘመናዊ የመስኖ ግብርና ከተጀመረ ከግማሽ ምዕተ አመት በላይ ቢሆንም ለብዙ ዓመታት ዘርፉ ትኩረት ሳያገኝ ቆይቷል፡፡ ሆኖም ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት በነበሩት አገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ዕቅዶች ማለትም የተፋጠነና ዘለቄታዊነት ያለውና ድህነትን የማጥፋት ዕቅድ አንድና ሁለት (PASDEP I and II) እንዲሁም የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንድና ሁለት (GTP I and II) ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ በነዚህ የፕላን ጊዜያት ሰፊ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም በተለይ የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ ከፍተኛ የቴክኒክና የኢንቨስትመንት አቅም የሚጠይቅ ከመሆኑና የዚህ አቅም ውስንነት ጋር ተያይዞ በሚፈለገው ፍጥነት ማልማት አልተቻለም፡፡

የውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች በመቅረፍ የተሻለ አፈጻጸም ማስመዝገብ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡ ሆኖም በመስኖ ልማት ሥራዎች ላይ አዘውትረው የሚታዩ ችግሮች ይኸውም በፕሮጀክቶች ጥናት ላይ ወጥ ያልሆነ አሰራርና የጥራት ችግር፣ በግንባታ ላይ የሚታዩ የጊዜ፣ በጀትና ጥራት ችግሮች እንዲሁም በአሰራር ላይ የሚታዩ የዝቅተኛ ምርታማነት፣ ውጤታማ ያልሆነ የውሀ አጠቃቀም፣ በቂ ያልሆነ የመስኖ አውታሮች አስተዳደርና ጥገና፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ያለመስራት እና

የመሳሰሉት ችግሮችን ትኩረት ሰጥቶ ለመፍታት እንዲቻል የዘርፉን አቅም በመገንባት የአገሪቱን የዕድገት ፍላጎት ያገናዘበ የመካከለኛና የረጅም ዕቅድ በመቅረጽ ዘርፉን በቁርጠኝነት እንዲመራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ይህንኑ ለመምራት እንዲቻል ይህ የአስር ዓመት (2013-2022) የመስኖ መሪ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.2 የመሪ ዕቅዱ አስፈላጊነት

ይህ መሪ ዕቅድ የዘርፉን አቅም በመገንባት እና የመስኖ ልማት ግንባታዎችን የአፈጻጸም ቅልጥፍና በጊዜና በወጪ እንዲሁም በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለማከናወን ብሎም ትኩረት በሚሹ የመስኖ ልማት ስራዎች ላይ የሚታዩ ዋና ዋና ችግሮች ላይ በማተኮር ችግሮችን ለመፍታት የሚስችል ዕቅድ በመቅረጽ ዘርፉ በቁርጠኝነት እንዲመራ ለማድረግ ነው፡፡

## 1.3 ዓላማ

የዚህ መሪ ዕቅድ ዋና ዓላማ የመስኖ ልማት ዘርፍ ሃገሪቱ ካቀደቻቸው የመካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገራት ተርታ ማሰለፍ፤ የአረንጋዴ ልማትን ማሳለጥ፤ የዘላቂ የልማት ግቦችን እንዲሁም የአፍሪካ 2063 አጀንዳዎችን ያገናዘበ ሆኖ በአግባቡ እንዲመራ ለማድረግ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- የመስኖ ልማት የማስፋፋት ስራ በአዳዲስ የልማት ኮሪደሮች በተቀናጀና በተቀላጠፈ መልኩ እንዲካሄድ ለማድረግ፤
- የመስኖ ልማት ለስራ ፈጠራ፤ ለኢንቨስትመንት እና ሃብት ማፍሪያነት ያለውን አስተዋፅኦ ለማጎልበት፤
- ለመስኖ ልማትና አስተዳደር አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር፤እና
- የመስኖ ፕሮጀክቶችን ምርታማነት ለመጨመርና ዘላቂነታቸውን ለማረጋገጥ፤

## 2. የመስኖ ዘርፍ ትንተና

### 2.1 ዘርፉ አሁን ያለበት ደረጃ

ዘመናዊ የመስኖ እርሻ በኢትዮጵያ የተጀመረው እንደ እ.ኤ.አ በ1950ዎቹ በአዋሽ ተፋሰስ ውስጥ ከአግሮ-ኢንዱስትሪ መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው፡፡ ከዚያ ወዲህ በተለያዩ ጊዜያት የማስተር ፕላን ጥናቶችን አገሪቱ ባላት ተፋሰሶች ላይ በአገር ውስጥና በውጭ ባለሙያዎችና ድርጅቶች በማስጠናት ለመስኖ ሊውል የሚችለውን የውሃና የመሬት ሃብቷን ለማወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህንንም መሰረት ባደረገ በተለያየ ደረጃ ሊለሙ የሚችሉ በርካታ የመስኖ ፕሮጀክቶችን በመለየት ከቅድመ ጥናት ጀምሮ እስከ ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን ደረጃ እንዲሰራ ማድረግ ተችሏል፡፡

ይህም ሆኖ የመስኖ ልማት በመንግስት ትኩረት ማነስና በተለያዩ ችግሮች በተለይም በዋናነት በአቅም ውስንነት (በሰው ሃይልና ፋይናንስ እጥረት) ምክንያት ለበርካታ አመታት እድገት ሳያሳይ ቆይቷል፡፡ ከባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት ወዲህ ግን መንግስት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠቱ የተነሳ የተሻለ እመርታ አሳይቷል፡፡ ለአብነት ያህል በ1982 ዓ.ም በአገሪቱ በመስኖ ይለማ ከነበረው 176,105ሄክታር መሬት በ 2010ዓ.ም ወደ 1.2 ሚሊዮን ሄክታር ደርሷል፡፡ ከዚህ ውስጥ ሰፋፊና መካከለኛ መስኖ አውታር በከፊልና ሙሉ በሙሉ የተገነባለት 490,000 ሄክታር ነው፡፡ ይህም ሆኖ የተገነቡት የመስኖ ተቋማት በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት እየሰጡ አይገኝም፡፡

በሌላ መልኩ እስከአሁን በመስኖ የለማው አጠቃላይ እየታረሰ ካለው 15 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ከ 8 ፐርሰንት ያነሰ ሲሆን የመስኖ አለኝታ ተብሎ ከሚገመተው ከ 5.8 እስከ 7.5 ሚሊዮን ሄክታር ውስጥ ደግሞ 20 ፐርሰንት ያህሉ ብቻ ነው፡፡ ይህም በተነፃፃሪነት ሲታይ አበረታች እድገት ቢሆንም አገሪቷ ካላት የውሃና የመሬት የማልማት አቅም አንፃር ግን እስከአሁን የመስኖ ልማቱ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም እንደምክንያት ከሚቀርቡ ዋና ዋና ችግሮች መካከል ውስን የሆነ ተቋማዊ አቅም፣ በመስኩ የሰለጠነ የሰው ሀይል እጥረት፣ የፋይናንስ አቅርቦት ዕጥረት፣ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፣ ውስን የቴክኖሎጂ አቅም እና የገበያ ትስስር መጥቀስ ይቻላል፡፡

ከላይ እንደተመላከተው የመስኖ ልማት ዘርፉን ለማስፋፋት ከ 2003 ዓ.ም ጀምሮ ሁለት ተከታታይ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች (ዕትዕ) ተነድፎ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተለይም በመጀመሪያው የዕትዕ (2003 — 2007) የከፍተኛና መካከለኛ

የመስኖ ጥናትና ዲዛይን እና ጥገና ስራዎች ጥሩ አፈፃፀም ቢኖርም በመስኖ ግንባታ ዘርፍ የነበረው የእቅድ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑ ተገምግሟል፡፡ የሁለተኛው ዕትዕ ዘመን (2008-2012) ከተጀመረ ጀምሮ እስከአሁን ባለው ሂደት ለፕሮጀክቶች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እና የተሻለ የክትትል እና ግምገማ ስራዎችን በማከናወን አብዛኞቹ ፕሮጀክቶች በዕቅድ ዘመኑ ለማጠናቀቅ ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ሲሆን በአጠቃላይ የፕሮጀከቶች የፊዚካል ስራዎች አፈፃፀም በተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡

በእስከአሁኑ በዘርፉ እያጋጠሙ ያሉትን በርካታ ችግሮች በተለይም ከግንባታ ስራዎች ጋር የተያያዙትን በከፊል በመቅረፍ ሥራዎችን ለመፈፀም እንዲቻል የተለያዩ ጥረቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች በማስቀመጥ ለመተግበር ተችሏል፡፡ ከነዚህም መከከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- ❖ ኮንትራክተሮች ተጨማሪ ማሽነሪዎችንና መሳሪያዎችን በኪራይና በግዢ እንዲያስገቡ ተደርጓል፡፡
- ❖ የግንባታ የስራ ሺፍት እንዲጨምር በማድረግ የግንባታ ስራዎች እንዲፋጠኑ ተደርጓል፡፡
- ❖ የሴክተር የአቅም ግንባታ ስራዎችን እንደ ፕሮግራም በመያዝ የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ ተችሏል፡፡
- ❖ ፕሮጀክቶች ከክልልና ፌደራል መንግስት በሚውጣጡ የጋራ ስቲሪንግና ቴክኒክ ኮሚቴዎች እንዲመሩና ቀልጣፋ ውሳኔዎች እንዲሰጡተደርጓል፡፡
- ❖ አንዳንድ ማሽነሪዎችና መሳሪያዎች በሃገር ውስጥ የሚመረቱበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

ሆኖም ከላይ የተጠቀሱት ጥረቶች ቢደረጉም የዘርፉ ልማት በሚፈለገው ደረጃ መፋጠን አልቻለም፡፡

## 2.2 ለዘርፉ ልማት ወሳኝ የሆኑ ሰብአዊና ቁሳዊ ሃብቶች

### 2.2.1 የሰው ሃብት

የአንድ ሀገር የመስኖ ልማት ውጤታማነት ሀገሪቱ በዘርፉ በሚኖራት ብቁ የሰው ኃይል ይወሰናል፡፡ በተለያዩ የመስኖ ልማትና ተጓዳኝ ስራዎች ላይ በሚሳተፉ የመንግስትና ክልል መስሪያ ቤቶች፣ የምርምርና ስልጠና ተቋማት እንዲሁም ዩኒቨርሲቲዎች ያለውን የሰው ኃይል የትምህርት ሁኔታ ስርጭትና ብዛት መረጃዎችን ትክክለኛ አህዝ ማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም በ 2009 ዓ.ም የተሰራውን የመስኖ ፍኖተ ካርታ ዋቢ በማድረግ የተገኘውን መረጃ በሙያ ዘርፍ በመከፋፈል በሰንጠረዥ 1 ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 1. በመስኖ ዘርፍ ተያያዥነት ያላቸው የባለሙያዎች ብዛት

| ባለሙያዎች | ድምር |
|---|---|
| ሲቪል ምህንድስና | 44843 |
| የውሀ ሀብት ምህንድስና | 18430 |
| የእርሻ ሳይንስ | 87905 |
| የእርሻ ኤክስቴንሽን | 17643 |
| የመስክ ሰብል ምርት | 2816 |
| ሆርቲካልቸር | 5570 |
| የእርሻ ኢኮኖሚክስ | 12633 |
| በከርሰ-ምድር ውሀ | 3494 |
| የውሀ ልኬት ተቆጣጣሪ | 126 |
| የጉድጓድ ውሀ ቁፋሮ | 2021 |
| **ጠቅላላ ድምር** | **195481** |

### 2.2.2 ቁሳዊ ሃብት

ለመስኖ ልማት ተስማሚ የሆነ መሬት እና በቂ የሆነ ውሃ ሃብት ወሳኝ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ለእርሻ የሚውል ከ40-60 ሚሊዩን ሄክታር የሚሆን መሬት እንዳላት ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ መሬት ውስጥ ያለውን የውሃ ሃብት ግምት ውስጥ በማስገባት ከ 5.8-7.5 ሚሊዩን ሄክታር ድረስ በመስኖ ሊለማ እንደሚችል በተለያየ ጊዜ የተደረጉ የመስኖ አለኝታ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በውሀ ሃብት በኩል አገሪቱ በአማካይ በዓመት ወደ 900 ቢሊዮን ኪ.ሜትር የሚሆን የዝናብ መጠን ታገኛለች፡፡ ከዚህ ውስጥ በ12 የአገሪቱ ተፋሰሶች በአመት 122 ቢሊዩን ኪዩቢክ ሜትር በገፀ-ምድር ውሃነት እንደሚለወጥ የተለያዩ የማስተር ፕላን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የከርሰ ምድር የውሃ ሃብት ክምችትን በተመለከተ ደግሞ የተለያዩ ጥናታዊ ግምቶች ቢኖሩም አገሪቱ ከ 36-40 ቢሊዩን ኪዩቢክ ሜትር የሚሆን ውሃ እንዳላት ይገመታል፡፡

## 2.3 የ SWOT እና PESTLE ትንተና

### ሰንጠረዥ 2. ውስጣዊ ትንተና (ጥንካሬዎችና ድክመቶች)

| ጉዳዮች | ጥንካሬዎች | ድክመቶች |
|---|---|---|
| አመራርና ተቋማዊ መዋቅር | • የውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ለዘርፉ ትኩረት መስጠቱ በመስኖ ልማት እድገት መፋጠን ላይ ያለው አዎንታዊ አስተዋፅኦ፤ | • ፕሮጀክቶችን ከእቅድ እስከ ትግበራ የመምራትና ማስፈፀም ተቋማዊ አቅም እጥረት መኖር፤<br>• የተቋም አደረጃጀት አለመረጋጋት እና ውሳኔ አሰጣጥ ድክመት፤<br>• የመስኖ ልማት ላይ የሚሰሩ የመንግስት ተቋማት የአሰራር አካሄድ መደራረብ በልማቱ ውጤታማነት ላይ ያመጣው አሉታዊ ተፅዕኖ፤<br>• ከላይ እስከ ታች ያለው የመስኖ ልማት መዋቅር ስንሰለት ግልፅነት የጎደለው መሆን፤<br>• በመስኖ ዘርፍ ላይ ያሉ ተዋናዮች መካከል ቅንጅታዊ አሰራርና አሳታፊነት ያለመኖር፤<br>• አገራዊ የመስኖ ፖሊሲና ስትራቴጂ ተፈጻሚነታቸው ዝቅተኛ መሆን፤<br>• ወጥነት የጎደለው የፖሊሲ አተረጓጎም፤ |
| አስተዳደርና ተቋም | • ዘርፉ በመስኩ በቂ እውቀትና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች መመራት መጀመሩ፤<br><br>• የመስኖ ጥናትና ግንባታ ስራ የሚሰሩ የፌዴራልና የክልል ተቋማት መኖራቸው፤ | • ነባር የመስኖ ፕሮጀክቶች ውጤታማነታአቸው ዝቅተኛ መሆን፤<br>• የመስኖ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን በበቂ ቅድመ ዝግጅት አለመጀመራቸውና የተጠኑትም ጥናታቸው በሚፈለገው የጥራት ደረጃ አለመሰራቱ፤<br>• የመስኖ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ወጥነት ባለው ስታንዳርድ አለመሰራቱ፤<br>• የመስኖ ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንዲሁም በሚፈለገው የጥራት ደረጃ አለመጠናቀቅ፤<br>• የመስኖ ልማት ስራን ጥራትና አስተዳደራዊ ስራዎችን የሚገመግም የተለየ ተቋም አለመኖር፤<br>• የመስኖ ልማት ስራ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ፈጥሮ አለመሄድ፤<br>• የመስኖ ተጠቃሚዎች የክፍያ ስርዓት አለመዘርጋት፤ |

| ጉዳዮች | ጥንካሬዎች | ድክመቶች |
| --- | --- | --- |
| | | • የመካከለኛና ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክት አውታሮችን የሚያስተዳድር ተቋማዊ አደረጃጀት አለመኖር፤<br>• የውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን የመመስረትና የማጠናከር ስራ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆን፤<br>• የመስኖ ልማት መርሃ-ግብሮች አሰራርና ጥገና ተገቢው ትኩረት አለመሰጠቱ፤<br>• የውሃ ተጠቃሚ ማህበራት ውስጥ በአባላትና በአመራር ደረጃ የሴቶችና አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ አናሳ መሆን፤<br>• የመስኖ ልማት ስራ ላይ በመስኩ የተማሩ ዜጎች ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ መሆን፤<br>• የመስኖ ልማት ዘርፍ በጥናትና ምርምር ውጤቶች አለመታገዙ፤<br>• የመስኖ ዘርፉን የሚመሩ ተቋማት ከዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ተቋማት ጋር በትብብር ያለመስራት፤<br>• የመስኖ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም በስፋት አለመተግበሩ፤<br>• ውስን የማስኖ ልማት የእውቀት ሽግግር፤<br>• ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች እና ዕቃዎች የጥራት ስታንዳርድ አለመኖር፤<br>• በመስኖ ዘርፍ የተሰማሩ አማካሪና የስራ ተቋራጮቾች የአቅም ውስንነት መኖር፤<br>• የአገሪቱ የመስኖ አለኝታ በውል አለመታወቅ በዕቅድ አዘገጃጀት ላይ ያለው ተፅዕኖ፤<br>• የመስኖ ልማት መረጃ ቋት ስርዓት አለመኖር፤ |
| የሰው ሃይል | • ለዘርፉ መጠናከር በመስኩ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው የዩኒቨርሲቲ የዘርፉ ባለሙያዎች ጋር በጋራ የመስራት እንቅስቃሴ መጀመሩ፤ | • በመስኩ በቂ ልምድና ክህሎት ያለው ባለሙያ እጥረት |
| ፋሲሊቲና ቁሳቁስ | • በውስን ደረጃም ቢሆን የላቦራቶሪ አገልግሎትና የቴክኒሺያን ማሰልጠኛ | • የመስኖ ጥናትና ዲዛይን የሚያግዝ የተጠናከረ ዘመናዊ ላቦራቶሪና ፋሲሊቲ እጥረትና ያሉትንም በአግባቡ አለመጠቀም፤ |

| ጉዳዮች | ጥንካሬዎች | ድክመቶች |
|---|---|---|
| | ተቋማት መኖራቸው፤<br>• ለሁሉም ተፋሰሶች የመስኖ ልማትን አቅጣጫ የሚያሳዩ ማስተር ፕላንና ተዛማጅ ጥናቶች (Growth Corridors) መኖራቸው፡ | |

## ሰንጠረዥ 3. ውጫዊ ትንተና (ምቹ ሁኔታዎችና ስጋቶች)

| ጉዳዮች | ምቹ ሁኔታዎች | ስጋቶች |
|---|---|---|
| ፖለቲካ | • ለዘርፉ የተለየ ትኩረት በመንግስት መሰጠቱ፤<br>• በዘርፉ ስልጠና የሚሰጡ የትምህርት ተቋማት መስፋፋት፤<br>• መንግስት ለመስኖ ዘርፍ ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት መፍቀዱ የፈጠረው ምቹ ሁኔታ፤ | • የመሬት አስተዳደርና ተያያዥ የአፈፃፀም ተግዳሮቶች በመስኖ ልማት ላይ ያለው አሉታዊ ተፅእኖ፤<br>• የመስኖ መሬት ክፍፍል የአፈፃፀም ችግር፤<br>• የጎረቤት ሃገሮች በሚገነቡ የመስኖ ግድቦች ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ፤<br>• የሃገራት ውስጣዊ ፖለቲካ ባላደጉት ሀገራት ላይ ያለው ተፅዕኖ፤ |
| ህጋዊነት | • ሀገራዊ የመስኖ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መኖር፤<br>• የግሉ ዘርፍ ከመንግስት ጋር በአጋርነት በተለያዩ የኢኮኖሚ ሴክተሮች እንዲሰማራ ምቹ ሁኔታዎች መፈጠሩ፤ | • የሚወጡ ህጎች በተጠቃሚው ዘንድ ተግባራዊ አለመደረግ፤<br>• የመሬት አስተዳደርና ተያያዥ የአፈፃጸም ተግዳሮቶች በመስኖ ልማት ላይ ያለው አሉታዊ ተፅእኖ፤ |
| ኢኮኖሚ | • የአገሪቷ የኢኮኖሚ እድገት ለዘርፉ መሻሻል አዎንታዊ አስተዋፅኦ ያለው መሆኑ፤<br>• ለመስኖ ልማት እየተመደበ ያለው በጀት እያደገ መምጣቱ፤<br>• የአግሮ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ለዘርፉ እድገት ያለው አስተዋፅኦ፤ | • ለዘርፉ ልማት በቂና አስተማማኝ ፋይናንስ አለመኖር፤<br>• የውጭ ምንዛሪ ዕጥረት፤<br>• የግል ባለሃብቱ በዘርፉ ለመሳተፍ ያለው ፍላጎት አናሳ መሆን፤<br>• የመስኖ መሬት ካሳ ክፍያ ጋር በተገናኘ የፕሮጀክት ዋጋ መናር፤<br>• የአለም ምጣኔ ሃብት መዋዠቅ፤<br>• ሙሉና ወጥ የሆኑ ድጋፎች ያለመኖር፤<br>• |

| ጉዳዮች | ምቹ ሁኔታዎች | ስጋቶች |
|---|---|---|
| | • የአገሪቱ አቀማመጥ ለአለም አቀፍ ገበያ ያለው ምቹነት፤<br>• የመሰረተ ልማት (መንገድ፤ መብራት፤ ስልክ) መሻሻልና መስፋፋት፤<br>• የተለያዩ አጋር ድርጅቶችና አገሮች ለዘርፉ እድገት የሚያደርጉት የገንዘብ ድጋፍ መሻሻል፤ | •<br>• |
| ማህበራዊ | • ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ከፍተኛ የስራ ሃይል እና የገበያ ምንጭነት፤<br>• ማህበረሰቡ ለመስኖ ዕድገት ያለው ፍላጎትና ድጋፍ፤ | • ከመስኖ ልማት ጋር ተያይዞ በመሬት ይዞታ ዙሪያ ሊፈጠር የሚችል ግጭት፤<br>• ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር በውሃ እና መሬት ላይ ሊያደርሰው የሚችለው አሉታዊ ጫና፤<br>• የተማረ ወጣት በመስኖ እርሻ ስራ መሰማራት አለመፈለግ፤<br>• የሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ማነስ በዘርፉ ላይ ሊያስከትለው የሚችለው ተፅዕኖ፤<br>• ከፍተኛ የሰው ሃይል ፍልሰት፤<br>• በአለም አቀፍ ደረጃ የመስኖ ልማት አደረጃጀቶች ወጥነት የጎደላቸው ሆኖ መታየት፤ |
| ቴክኖሎጂ | • ዘርፉን ሊያግዙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች በከፍተኛ ደረጃ እያደጉ መምጣታቸው፤<br>• ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ዕውቀትና ልምድን የተሻለ ተሞክሮ ካላቸው አገሮች መውሰድ መቻሉ፤ | • የመስኖ ቴክኖሎጂ ግብአቶች በአገር ውስጥ ለማምረት ያለው የአቅም ውስንነትና የሚመረተውም በቂ ገበያ ማጣት፤<br>• ውስን የቴክኖሎጂ ፓኬጆችን ለገቢያ ማቅረብ በተለይም የስራ እድሜያቸው ውስን መሆን፤<br>• የእርሻ ስራ ዘመናዊ ስርዓት የተከተለ አለመሆን፤ |
| ኢንቫይርመንታል | • ለመስኖ ልማት ተስማሚና ሰፊ መሬት በተለይም በዝቅተኛ ቦታዎች መኖር፤<br>• በቂ የገፀ-ምድርና ከርሰ-ምድር ውሃ መኖር | • የአየር ንብረት መዛባት በዘርፉ ላይ ያለው ተፅዕኖ፤<br>• በአለም መድረክ ላይ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የተደረጉ ውይይቶች ወደ ትግበራ አለመግባት፤ |

## 3. የባለድርሻ አካላት ትንተና

የመስኖ ልማት ዘርፍ የውስጥና የውጭ ባለድርሻ አካላት አሉት፡፡ እነዚህ አካላት የራሳቸው የሆነ ድጋፍና አስተዋፅኦ ሲኖራቸው ይህንን በሶስት ደረጃ ማለትም ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ በማለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት ሁለቱንም በማቀናጀት የባለድርሻ አካላቱ ከዘርፉ ጋር ያላቸው የግንኙነት ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ የባለድርሻ አካላቱ ዝርዝር እና በልማቱ ላይ የሚያሳደሩት ተፅዕኖ እና ድጋፍ በሰንጠረዥ 4 በዝርዝር ቀርቧል፡፡



ሰንጠረዥ 4. የመስኖ ልማት ዘርፍ ባለድርሻዎች ዝርዝርና ፍላጎት

| የባለድርሻዎች ዝርዝር | የባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ | | የባለድርሻ አካላት ድጋፍ | | የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ (1-ዋና ባለድርሻ/ 2-ተጽእኖ የጎላ/ 3-መካከለኛ/ 4-መረጃ/ 5-ዝቅተኛ) | ከተቋሙ የሚጠበቅ ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | የድጋፍ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | | |
| **ሀ. የውስጥ ባለድርሻዎች** | | | | | | |
| 1) የመስኖ ልማት ኮሚሽን | ከፍተኛ | የእቅዱ ፈጻሚነት | ከፍተኛ | ፈጣን፣ ውጤታማ እና የተቀላጠፈ የመስኖ ልማት ማካሄድ | ዋና ባለድርሻ | • ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠር<br>• የአቅም ግንባታ መስጠት<br>• የአሰራር መመሪያና ስታንዳርዶች ማዘጋጀት<br>• የመካከለኛና ከፍተኛ መስኖ ፕሮጀክቶችን መለየት፣ ጥናትና ዲዛይን መስራት፤ መገንባት፤ ማስተዳደር እና ጥገና ማድረግ |
| 2) የውሃ ልማት ኮሚሽን | ዝቅተኛ | ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ | ከፍተኛ | የፕሮጀክት ተጠቃሚ | መረጃ ግንኙነት | • ፕሮጀክቶች በተቀናጀ ውሃ ሀብት ልማት መርህ ማቀድና መተግበር |
| 3) የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን | ከፍተኛ | • በተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ<br>• በውሃ አካላት ጥበቃና እንክብካቤ<br>• በመስኖ ውሃ ፍትሃዊ ክፍፍል | ዝቅተኛ | • ለተቀናጀ ተፋሰስ አስተዳደር ትግበራ | ተጽዕኖ የጎላ | • ፕሮጀክቶች በተቀናጀ ውሃ ሀብት ልማት መርህ ማቀድ<br>• ጠንካራ መረጃ ልውውጥ መዘርጋት |
| 4) ብሔራዊ ሜቴዎሮሎጂ አግልግሎት ድርጅት | መካከለኛ | • የአየር ንብረት መረጃ አቅርቦት | ከፍተኛ | የተቋሙን የአየር ንብረት መረጃ አገልግሎት መጠቀም | መካከለኛ | • የአየር ንብረት መረጃ ጥያቄ በወቅት አዘጋጅቶ ማቅረብ፣ ይህንንም መሰረት አድርጎ ማቀድ |
| 5) የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ | መካከለኛ | በዘመናዊ መስኖ ልማት ያለው ከፍተኛ | ዝቅተኛ | • የሚፈለገው ሀይል ከፍተኛ | ዝቅተኛ ድርሻ | • የፕሮጀክቶች ኤልክትሪክ ሀይል ፍላጎት መረጃ በወቅት ማዘጋጀት፣ |

| የባለድርሻዎች ዝርዝር | የባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ | | የባለድርሻ አካላት ድጋፍ | | የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ (1-ዋና ባለድርሻ/ 2-ተጽእኖ የጎላ/ 3-መካከለኛ/ 4-መረጃ/ 5-ዝቅተኛ) | ከተቋሙ የሚጠበቅ ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | የድጋፍ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | | |
| አገልግሎት | | የሀይል ፍላጎት | | መሆንና አቅርቦት ውስንነት | | አስፈላጊው በጀት መመደብ |
| 6) የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት | ዝቅተኛ | በመስኩ የሚሰጠው ስልጠና አቅርቦት አገልግሎት | ከፍተኛ | በመስኩ የሚሰጥ ስልጠና | መረጃ ግንኙነት | • የሰው ሀብት አቅም ግንባታ ስልጠና ለማከናወን ከተቋሙ ጋር ማቀድና አስፈላጊው ድጋፍ ማድረግ |
| **ለ. የውጭ ባለድርሻዎች** | | | | | | |
| 1) የተወካዮች ም/ቤት እና<br>2) የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት | ከፍተኛ | • ፖሊሲና ስታራቴጂ በማውጣት<br>• በፕሮጀክት እቅድ ውሳኔ ሰጭነት<br>• በጀት በመመደብ<br>• በክትትልና ድጋፍ | ከፍተኛ | ➢ የመስኖ ፕሮጀክቶች ያላቸው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ና ማህበራዊ ጥቅም | ª“ vKÉ`h | • አዋጭነታቸው የታመነባቸውና ለወጣቶች የስራ ዕድል የሚፈጥሩ፤ ህብረተሰብን በፍትሃዊነት ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክቶችን መቅረፅ፤<br>• ውቅታዊ የሆነ ዕቅድና ሪፖርት የሚቀርብበት ስርዓት መፍጠር፤<br>• የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀት ጊዜና ጥራት እንዲጠናቀቁ ማስቻል፤ |
| 3) የገንዘብ ሚ/ርና የፕላን ልማት ኮሚሽን | ከፍተኛ | • ፕሮጀክት በማጽደቅ<br>• የተመደበውን በጀት በመልቀቅ<br>• በእቅድና አፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ | ከፍተኛ | ➢ የመስኖ ፕሮጀክቶች ያላቸው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ና ማህበራዊ ጥቅም | ዋና ባለድርሻ | • አዋጭነታቸው የታመነባቸውና ህብረተሰብን በፍትሃዊነት ተጠቃሚ የሚያርጉ ፕሮጀክቶችን መቅረጽ<br>• ወቅታዊ የሆነ እቅድና ሪፖርት የሚቀርብበት ስራዓት መዘርጋት<br>• የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀት፣ ጊዜ እና |

| የባለድርሻዎች ዝርዝር | የባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ | | የባለድርሻ አካላት ድጋፍ | | የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ (1-ዋና ባለድርሻ/ 2-ተጽእኖ የጎላ/ 3-መካከለኛ/ 4-መረጃ/ 5-ዝቅተኛ) | ከተቋሙ የሚጠበቅ ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | የድጋፍ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | | |
| | | | | | | ጥራት እንዲጠናቀቁ ማስቻል<br>• የተፈቀደን በጀት በእቅዱ መሰረት ስራ ላይ ማዋል |
| 4) የውጭ ጉዳይ ሚ/ር | መካከለኛ | ➢ የፋይናንስና ቴክኒክ የውጭ ድጋፍ በማፈላለግ | መካከለኛ | ➢ የወሰን ተሻጋር ወንዞች መስኖ ልማት ጉዳዮች ምክክር<br>➢ የፋይናንስና የቴክኒክ የውጭ ድጋፍ ማፈላለግ<br>➢ በመስኖ ልማትበውጭ ባለሀብቶች ና መንግስታት ተሳታፎ | መካከለኛ | • አስፈላጊውን የፋይናንስ፣ ቴክኒክና ሌሎች አቅም ግንባታዎች የውጭ ድጋፍ ፍላጎቶችን ማሳወቅ<br>• የወሰን ተሻጋር ወንዞች መስኖ ልማት ፕሮግራሞች ሲታቀዱ ማሳተፍና መረጃ በወቅቱ ማቅረብ<br>• በውጭ ባለሀብቶች ና መንግስታት ትብብር ሊለሙ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ለይቶ ማቅረብ፣ በመድረኮች ላይ ተገኝቶ ማስተዋወቅ |
| 5) የአካባቢና የአየር ለውጥ ኮሚሽን | መካከለኛ | የሚቀረጹ ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅኖዎች ጥናት ማጽደቅ | መካከለኛ | • የግንባታ ወቅት መስኖ ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅኖዎች ከፍተኛ ቢሆንም በሌላ በኩል አወንታዊ ጥቅም ስላላቸው | መካከለኛ | • በፕሮጀክት ጥናቶች የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅኖዎች በጥልቀት እንዲጠና ማድረግ<br>• የትግበራ ጠንካራ ክትትል |
| 6) የግብርና ሚኒስቴር | ከፍተኛ | ➢ የመስኖ ግንባታዎች ወደ | ከፍተኛ | • የመስኖ ልማት ምግብ ዋስትና | ዋና ባለድርሻ | • የምግብ ዋስትና የሚያረጋግጡ ቀርጾ ወደ ልማት መግባት |

| የባለድርሻዎች ዝርዝር | የባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ | | የባለድርሻ አካላት ድጋፍ | | የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ (1-ዋና ባለድርሻ/ 2-ተጽእኖ የጎላ/ 3-መካከለኛ/ 4-መረጃ/ 5-ዝቅተኛ) | ከተቋሙ የሚጠበቅ ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | የድጋፍ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | | |
| | | ልማት ማስገባት<br>➢ የመስኖ ልማት ምርታማነታቸው መጨመር<br>➢ የግብርና መረጃዎች በወቅቱ ማቅረብ | | ለማረጋገጥ ያለው ከፍተኛ ሚና | | • ወቅታዊ የመስኖ ልማት እቅድና መረጃዎች መለዋወጥ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት |
| 7) ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ዝቅተኛ | ተጠቃሚ | ከፍተኛ | • የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ከኢንዱስት ፓርኮች ጋር ትስስር ለመፍጠር | መረጃ ግንኙነት | • የኢንዱስትሪ ግብአቶች በአገር ውስጥ አቅም መመረት የሚያስችልና ከኢንዱስት ፓርኮች ጋር ትስስር ያላቸው ፕሮጀክቶች ቀርጾ ወደ ልማት መግባት |
| 8) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር | መካከለኛ | የኢኖቬሽንና የመስኖ ቴክኖሎጂ ልማት አገልግሎት መስጠት | ከፍተኛ | • የመስኖ ልማት ዘመናዊ ለማድረግ የሚጠይቀው ቴክኖሎጂ በአገር ውስጥ ለማምረት ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ላይ የሚሰጡ ድጋፎች | መካከለኛ | • መስኖ ልማቱን የሚያዘምኑ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮችን በጋራ እቅድ ይዞ መተግበር |
| 9) የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | ዝቅተኛ | ዘርፉን ያለበትን ውስንነቶችን ለመቅረፍ የሚሰሩና የተሰሩ ምርምሮች መረጃ መስጠት | ከፍተኛ | • ዘርፉን ያለበትን ውስንነቶችን ለመቅረፍ የሚሰሩ ምርምሮች | መረጃ ግንኙነት | • በዘርፉ ላይ ያሉ ውስንነቶችን ለይቶ ለመቅረፍ የሚሰሩ ምርምሮችን መደገፍ |

| የባለድርሻዎች ዝርዝር | የባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ | | የባለድርሻ አካላት ድጋፍ | | የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ (1-ዋና ባለድርሻ/ 2-ተጽእኖ የጎላ/ 3-መካከለኛ/ 4-መረጃ/ 5-ዝቅተኛ) | ከተቋሙ የሚጠበቅ ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | የድጋፍ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | | |
| | | | | ያላቸው ከፍተኛ ጥቅም | | |
| 10) የግብርና ትርንስፎርሜሽን ኤጀንሲ | ዝቅተኛ | መስኖ ልማትን ለማዘመንና ውስንነቶችን ለመቅረፍ የሚደረጉ ጥናቶች እና ተሞክሮዎች መረጃ መስጠት | ከፍተኛ | • ዘርፉን ለማዘመንና ውስንነቶችን ለመቅረፍ የሚሰሩ ምርምሮች ያላቸው ከፍተኛ ጥቅም | መረጃ ግንኙነት | • በዘርፉ ላይ ያሉ ውስንነቶችን መለየት ለመቅረፍ እና ዘርፉን ለማዘመን የሚሰሩ ስራዎችን መደገፍ<br>• በዘርፉ የሰው ሀብት ልማትና አቅም ግንባታ ማከናወን |
| 11) የሳይንስና ከፍተኛ ት/ት ሚኒስቴርና ዩኒቨርስቲዎች | ዝቅተኛ | • መስኖ ልማትን ለማዘመንና ውስንነቶችን ለመቅረፍ የሚደረጉ ጥናቶች ምርምሮችና እና ተሞክሮዎች መረጃ መስጠት<br>• በዘርፉ የሰው ሀብት ልማት ማከናወን | ከፍተኛ | • ዘርፉን ለማዘመንና ውስንነቶችን ለመቅረፍ የሚሰሩ ጥናቶች ምርምሮችና እና ተሞክሮዎች ያላቸው ከፍተኛ ጥቅም<br>• የሰው ሀብት ልማት በማከናወን | መረጃ ግንኙነት | • በዘርፉ ላይ ያሉ ውስንነቶችን በመለየት ለመቅረፍ እንዲሁም ዘርፉን ለማዘመን የሚሰሩ ጥናቶች ምርምሮችና እና ተሞክሮዎች መደገፍ<br>• በዘርፉ የሰው ሀብት ልማትና አቅም ግንባታ በእቅድ ይዞ ማከናወን |
| 12) የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን | ዝቅተኛ | በፕሮጀክቶች ዙሪያ የመንገድ መሰረተ ልማት ፍላጎት መረጃ ማወቅ | መካከለኛ | በመስኖ ልማት ፕሮጀክት አካባቢ የሚከናወን መንገድ መሰረተ ልማት አገልግሎት | ዝቅተኛ ድርሻ | • በፕሮጀክቶች ዙሪያ የመንገድ መሰረተ ልማት ፍላጎት መረጃ ጥያቄ ማደራጀት ና ማቅረብ<br>• በልማት የሚነሱ የመንገድ መሰረተ ልማት መረጃ በወቅቱ አደራጅቶ ማቅረብ |

| የባለድርሻዎች ዝርዝር | የባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ | | የባለድርሻ አካላት ድጋፍ | | የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ (1-ዋና ባለድርሻ/ 2-ተጽእኖ የጎላ/ 3-መካከለኛ/ 4-መረጃ/ 5-ዝቅተኛ) | ከተቋሙ የሚጠበቅ ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | የድጋፍ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | | |
| | | | | | | |
| 13) የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ | ከፍተኛ | • በግዥ ጉዳይ ምክር አገልግሎት በመስጠት<br>• የግዥ ጉዳይ ቁጥጥር | መካከለኛ | • በግዥ ጉዳይ በሚሰጥ አገልግሎት | መካከለኛ | • የተቋሙ የግዥ ፍላጎት እቅድ በወቅቱ አዘጋጅቶ ማቅረብ<br>• በስፔስፊኬሽን መሰረት ጥራት ያላቸው እቃዎች ግዥ እንዲከናወን ክትትል ማድረግ<br>• ግዥዎች የአገሪቱን ግዥ መመሪያና ደንብ ተከትለው እንዲከናወኑ ማድረግ<br>• የማማከር አገልግሎት እና ልዩ ፍቃድ ጥያቄ በተገቢው መንገድ በወቅቱ ማቅረብ |
| 14) የሴቶችና ህጻናት ሚ/ር | ዝቅተኛ | የሴቶች፣ የወጣቶችና የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት መረጃ | ዝቅተኛ | የሴቶች፣ የወጣቶችና የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት መረጃ | ዝቅተኛ ድርሻ | • በመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ውስጥ የሴቶች፣ የወጣቶችና የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት ማካተት ፣ |
| 15) የወጣቶች ስራ እድል ፈጠራ ኤጀንሲ | ዝቅተኛ | የወጣቶችና ስራ እድል ፈጠራ መረጃ | ዝቅተኛ | የወጣቶችና ስራ እድል ፈጠራ መረጃ | ዝቅተኛ ድርሻ | • በዘርፉ ለተማሩ ወጣቶች በመስኖ ልማት ላይ ስራ እድል ለመፍጠር የሚያስችሉ ፕሮግራሞች መቅረጽና መተግበር |
| 16) የፈርጀብዙና የሁለትየሽ ለጋሽና አበዳሪ አገራትና ድርጅቶች | መካከለኛ | የእርዳታና ብድር ገንዘብ መድቦ በወቅቱ በመልቀቅ | መካከለኛ | • የህብተሰብ ተጠቃሚነት<br>• የተመደበው እርዳታና ብድር ህግና ደንብ ተከትሎ መዋል | መካከለኛ | • ጠንካራ የፕሮጀክት አስተዳደር ማዋቀር<br>• የተመደበው እርዳታና ብድር ህግና ደንብ ተከትሎ ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ<br>• የተሟላ መረጃና፣ አፈጻጸም ሪፖርት በወቅቱ ማቅረብ<br>• ፕሮጀክቶች በወቅቱ፣ ጥራታቸውን |

| የባለድርሻዎች ዝርዝር | የባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ | | የባለድርሻ አካላት ድጋፍ | | የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ (1-ዋና ባለድርሻ/ 2-ተጽእኖ የጎላ/ 3-መካከለኛ/ 4-መረጃ/ 5-ዝቅተኛ) | ከተቋሙ የሚጠበቅ ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | የድጋፍ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | | |
| | | | | | | ጠብቀው እንዲጠናቀቁ እና የህብተሰቡን ተጠቃሚነት እንዲያረጋግጡ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት |
| 17) የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን | ዝቅተኛ | መረጃ ተጠቃሚ | ከፍተኛ | ለስኳር ልማት የሚውሉ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ | መረጃ ግንኙነት | • ለስኳር ልማት በሚውል መስኖ ፕሮጀክት ተቀናጅቶ ማቀድና መስራት |
| 18) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ | ከፍተኛ | • ለተማሩ ወጣቶች መስኖ ልማት ብድር አቅርቦት<br>• ለግሉ ሴክተር ተሳትፎ አስፈላጊ ብድር አገልግሎት | መካከለኛ | የመስኖ ልማት ያለው አገራዊ ፋይዳ ከፍተኛ ቢሆንም የግሉ ሴክተር ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን | ተጽዕኖ የጎላ | • ለተማሩ ወጣቶች መስኖ ልማት እና ለግሉ ሴክተር ተሳትፎ ለማሳደግ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍ ማድረግ |
| 19) የክልል ዞንና ወረዳ መስ/ር ጽ/ቤቶች<br><br>20) የክልል ዞንና ወረዳ ውሃ፣ መስኖ፣ ግብርና መሬት አስተዳደር ስራ እድል ፈጠራ ጽ/ቤቶች | ከፍተኛ | • ፕሮጀክት ልየታ እና ጥናት<br>• በህብረተሰብ ተሳትፎ እና ተቀባይነት<br>• በግንባታ አፈጻጸም<br>• በመልሶ ማቋቋም<br>• በተቋም አስተዳደር | ከፍተኛ | • ፕሮጀክት ልየታ እና ጥናት ንቁ ተሳታፊነት<br>• ለህብረተሰብ ግንዛቤ በማስጨበጥ<br>• በግንባታ ክትትልና ድጋፍ<br>• የግንባታ ቦታ ነጻ በማድረግ፣በግንባ ታ ጥሬ እቃ አቅርቦት በማገዝ | ዋና ባለድርሻ | • በፕሮጀክት እቅድ እና ተግበራ ላይ ክልሎችን ተሳታፊ ማድረግ<br>• ፕሮጀክቶች ሲቀረጹና ሲጠኑ የአካባቢና ማህበረሰብ ልማት እንዲያካትቱ ማድረግ<br>• ተከታታይነት ያለው የግንኙነት መድረክ መፍጠርና መግባቢያ ሰነድ መፈራረም፣ ትግበራውን በጋራ መገምገም<br>• ፕሮጀክቶች በወቅቱ፣ ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲጠናቀቁ እና የህብተሰቡን ተጠቃሚነት |

| የባለድርሻዎች ዝርዝር | የባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ | | የባለድርሻ አካላት ድጋፍ | | የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ (1-ዋና ባለድርሻ/ 2-ተጽእኖ የጎላ/ 3-መካከለኛ/ 4-መረጃ/ 5-ዝቅተኛ) | ከተቋሙ የሚጠበቅ ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | የድጋፍ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | | |
| | | | | • የካሳ ክፍያና መልሶ ማቋቋም በወቅቱ በማከናወን<br>• ተቋሙን ተረክቦ በተገቢው ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጥ በማስቻል | | እንዲያረጋግጡ ጠንካራ ክልሎችን ተሳታፊ ያደረገ ክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት<br>• በፕሮጀክት ምክንያት ተነሺ ለሆኑ አካላት ተገቢ ካሳና የስራ ዋስትና ማረጋገጥ<br>• ፕሮጀክቶች ለወጣቶች እና ሴቶች ስራ እድል ተጠቃሚ እንዲያደርግ የሚያስችሉ ስራዎች መስራት<br>• አስፈላጊ የአቅም ግንባታ እንዲያገኙ ማድረግ |
| 21) የስራ ተቋራጭና አማካሪዎች | ከፍተኛ | • ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት<br>• ፕሮጀክቶች በታቀደው ጊዜ በማጠናቀቅ | ከፍተኛ | • በዘርፉ የሚፈጠር ስራ እድል<br>• አቅም ለማዳበር | ዋና ባለድርሻ | • በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች አቅማቸው እንዲጎለብት የአቅም ግንባታና ማበረታቻ እንዲያገኙ የሚያስችሉ ስራዎች መስራት<br>• ግዥዎች ፍትሃዊና ሁሉንም አሳታፊ ባደረገ መልኩ እንዲከናወን ማድረግ<br>• የጥናት ግብዓት መረጃ/ዳታ/ ማደራጀት፣ ከሚመለከታቸው ተያያዥ አካላት ጋር በጋራ መስራት<br>• የተጓደሉ መመሪዎች እንዲሟሉ ማድረግ<br>• የጥናትና ዲዛይን ሰነድ በተሟላ ሁኔታ ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲከናወኑ የሚያስችል ስርዓት |

| የባለድርሻዎች ዝርዝር | የባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ | | የባለድርሻ አካላት ድጋፍ | | የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ (1-ዋና ባለድርሻ/ 2-ተጽእኖ የጎላ/ 3-መካከለኛ/ 4-መረጃ/ 5-ዝቅተኛ) | ከተቋሙ የሚጠበቅ ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | የድጋፍ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | | |
| | | | | | | መዘርጋት<br>• ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ሊሰጥ የሚያስችል ዘመናዊና ቀልጣፋ አሰራር ስርዓት መዘርጋት |
| 22) በመስኖ ልማት የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች | ዝቅተኛ | የመስኖ ልማት ተጠቃሚ | ከፍተኛ | • በዘርፉ የሚኖር ስራ እድል<br>• በዘርፉ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች አቅም እንዲጎለብት<br>• ዘመናዊ እርሻ ለማስፋፋት<br>• አስተማማኝ የመስኖ ውሃ አቅርቦት | መረጃ ግንኙነት | • በዘርፉ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች አቅማቸው እንዲጎለብት የአቅም ግንባታና ማበረታቻ ለማግኘት የሚያስችሉ ስራዎች መስራት<br>• ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ሊሰጥ የሚያስችል ዘመናዊና ቀልጣፋ አሰራር ስርዓት መዘርጋት<br>• አስተማማኝ የመስኖ ውሃ አቅርቦትና የመስኖ አውታሮች ጥገና የሚያከናውን ስርዓት መዘርጋት<br>• በአሰራር ላይ የማማከርና የቴክኒካል ድጋፍ መስጠት እንዲሁም ዘመናዊ የመስኖ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ<br>• የመስኖ ልማት የተሟላ መረጃ ስርዓት መዘርጋት |
| 23) የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ | ከፍተኛ | ለዘላቂ መስኖ ልማት የህብረተሰብ ተሳትፎ | ከፍተኛ | • የመስኖ መሬት ተጠቃሚነት | ዋና ባለድርሻ | • በፕሮጀክት እቅድ እና ተግበራ ላይ ተሳታፊ ማድረግ |

| የባለድርሻዎች ዝርዝር | የባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ | | የባለድርሻ አካላት ድጋፍ | | የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ (1-ዋና ባለድርሻ/ 2-ተጽእኖ የጎላ/ 3-መካከለኛ/ 4-መረጃ/ 5-ዝቅተኛ) | ከተቋሙ የሚጠበቅ ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | የድጋፍ ደረጃ (ከፍተኛ/ መካከለኛ /ዝቅተኛ) | ምክንያት | | |
| ማኀበራትና አርሶ አደሮች | | ከፍተኛ ድርሻ አስፈላጊነት | | • ከፍተኛ ምርት<br>• አስተማማኝ የመስኖ ውሃ አቅርቦት | | • ፕሮጀክቶች ሲቀረጹና ሲጠኑ የአካባቢና ማህበረሰብ ልማት እንዲያካትቱ ማድረግ<br>• የአቅም ግንባታና ማበረታቻ ለማግኘት የሚያስችሉ ስራዎች መስራት<br>• ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ሊሰጥ የሚያስችል ዘመናዊና ቀልጣፋ አሰራር ስርዓት መዘርጋት<br>• ማህበራትን በማቋቋምና ማደራጀት<br>• አስተማማኝ የመስኖ ውሃ አቅርቦትና የመስኖ አውታሮች ጥገና የሚያከናውን ስርዓት መዘርጋት<br>• በአሰራር ላይ የማማከርና የቴክኒካል ድጋፍ መስጠት እንዲሁም ዘመናዊ የመስኖ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ<br>• የመስኖ ልማት የተሟላ መረጃ ስርዓት መዘርጋትዘመናዊ የመስኖ ቴክኖሎጂ ማግኘት |

### ሰንጠረዥ 5 የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ ማጠቃለያ

| የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ደረጃ | ባለድርሻ አካላት | |
|---|---|---|
| ዋና ባለድርሻ | • የመስኖ ልማት ኮሚሽን<br>• የግብርና ሚ/ር<br>• ሠራተኛና ማኔጅመንት<br>• ተወካዮች ም/ቤት<br>• ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>• የገንዘብ ሚ/ር | • ፕላን ልማት ኮሚሽን<br>• የክልል ዞንና ወረዳ መስ/ር ጽ/ቤቶች፣የክልል ዞንና ወረዳ ውሃ፣ መስኖ፣ ግብርና መሬት አስተዳደር ስራ እድል ፈጠራ ጽ/ቤቶች<br>• የስራ ተቋራጭና አማካሪዎች<br>• የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማኀበራትና አርሶ አደሮች |
| ተጽዕኖ የኀላ | • የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን | • የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ |
| መካከለኛ | • የውጭ ጉዳይ ሚ/ር<br>• የአካባቢና የአየር ለውጥ ኮሚሽን<br>• የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚ/ር | • የመልቲ ላተራልና የባይላተራል ዕርዳታ ሰጪና አበዳሪ ሃገራትና ድርጅቶች<br>• የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ |
| መረጃ | • የውሃ ልማት ኮሚሽን<br>• ብሄራዊ ሜቲዎሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት<br>• የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት<br>• የኢንዱስትሪ ሚ/ር | • የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት<br>• የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ<br>• የሳይንስና ከፍተኛ ት/ት ሚኒስቴርና ዩኒቨርስቲዎች<br>• የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን<br>• በመስኖ ልማት የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች |
| ዝቅተኛ ድርሻ | • የኢትየጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኢትየጵያ መንገዶች ባለስልጣን | • የሴቶችና ህጻናት ሚ/ር<br>• የወጣቶች ስራ እድል ፈጠራ ኤጀንሲ |

# 4. የመስኖ ልማት ዘርፍ የስራ ድርሻና የሌሎች አገሮች ተሞክሮ ትንተና

## 4.1 በዘርፉ የሚሰሩ ስራዎች

በአገሪቱ በመስኖ ልማት ዘርፍ የሚከናወኑ ዋና ዋና ስራዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የመስኖ ፕሮጀክቶች የመለየት፣ ጥናትና የዲዛይን ስራ ማከናወን፤
2. የውሃ ሀብቱንና በመስኖ ሊለማ የሚችለውን የመስኖ መሬት መሠረት በማድረግ በተለይም በቆላማና ዝናብ አጠር አካባቢዎች የመስኖ ልማት ማስፋፋት፤
3. የተገነቡ የመስኖ ግድቦችን እና ውቅሮችን የማስተዳደር፤
4. በመስኖ ልማት የጥናት፤ የዲዛይንና የግንባታ ሥራዎች የግሉ ሴክተር እንዲሳተፍ ማበረታታት፤
5. የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ምርታማነትን በሚያሳድጉ በወቅታዊ ቴክኖሎጂዎች እንዲደገፉና ውሃ ቆጣቢ አሠራር እንዲከተሉ ማበረታታት፤
6. የመስኖ ልማት ሽፋን እንዲያድግ የሚያደርግ የአሰራር፤ መረጃና ኢንፎርሜሽን ሥርአት መዘርጋት፤
7. የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በተለያዩ የፋይናንስ ምንጮች እንዲታገዙ ማድረግ፤
8. በግብርናና ተያያዥ የሙያ ዘርፎች የተማሩ ወጣቶችን በገበያ ተኮር መስኖ ልማት እንዲሳተፉ ማድረግ፤
9. በመስኖ ልማት የሴቶች፣ የወጣቶችና የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ እንዲካተቱ በማድረግ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ ማድረግ፤
10. በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች፣ አማካሪና ተቋራጭ ድርጅቶች፣ እና ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በመስኖ ልማት ስራ አቅማቸው እንዲገነቡ ማድረግ፤

## 4.2 የመስኖ ልማት ዘርፍ የስራ ማዕቀፍና ተጓዳኝ ፖሊሲዎች

የመስኖ ልማት ዘርፍ አገራዊ የልማት ፖሊሲዎችን ያገናዘበ የመስኖ ልማት ማዕቀፍ አለው፡፡ የዚህ ማዕቀፍ ዋነኛ ግቡ ድህነትን ቅነሳ እና የአገር ኢኮኖሚን ማሳደግ ነው፡፡ ይህም ሲባል የመስኖ ልማት ፖሊሲ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከበርካታ የሃገሪቱ የልማት ፖሊሲዎች ጋር መስተጋብር ያለው ነው፡፡ ከመስኖ ዘርፍ ጋር ትስስር ያላቸውን ሁሉንም ፖሊሲዎች መዘርዘር ባይቻልም ቁልፍ የሆኑት ፖሊሲዎች ከዚህ በታች በአጭሩ ተዳስሰዋል፡፡

1. **የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፡-** የሃገሪቱ የፖሊሲ ምንጭ የሆነው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በመስኖ ዘርፍ ለሚሰሩ የልማት ስራዎች ግልፅ የሆኑ አንቀፆችን ያስቀምጣል፡፡ በተለይም ከመስኖ ስራ ጋር ተያይዞ የአካባቢ ጥበቃ ፣ ዘላቂ አጠቃቀምና እንክብካቤ በአንቀጽ 44 እና 92 በሰፊው ተቀምጠዋል፡፡ ይህም የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት እና ዘላቂነትን የሚያግዝ ነው፡፡
2. **የውሃ ሀብት ፖሊሲ፡-** በመስኖ ዘርፍ ለሚከናወኑ ስራዎች የውሃ ሀብት ፖሊሲ ዋነኛው ሲሆን፡ አጠቃላይ ግቡም ለኢኮኖሚያዊ ልማትና ዘላቂ ልማት የውሃ አቅርቦትን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ ለማድረግ ፊርጀ ብዙ ብሔራዊ ጥረቶችን ማጎልበት እና ማሳደግ ነው፡፡
3. **የመስኖ ፖሊሲ፡-** በዋናነት የመስኖ ፖሊሲ የውሃ ሃብቶች ኣካል ሲሆን አጠቃላይ አላማው ለምግብ ሰብሎች እና ለአግሮ ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ጥሬ እቃዎችን በብቃት እና ዘላቂ በሆነ መሠረት ለማምረት ያለመ ነው፡፡
4. **የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ፡-** የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ ከፍተኛ የሆነ ድጋፍ ለመስኖ ልማት እንደሚሰጥ ይታወቃል፡፡ የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ ዋና ዓላማዎች በምግብ ራስን ለመቻል የምግብ ሰብል ምርትን ማሳደግ፣ በግብርናው ዘርፍ ዘላቂ ልማት በማምጣት የገጠር ማህበረሰብ ኑሮን ማሻሻል፣ በኢንዱስትሪ የሚመሩ የግብርና ምርቶችን ማስፋፋት እና የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃን እውን የሚያደርግ የግብርና ልምድን በማስተዋወቅ ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ ናቸው፡፡
5. **የአካባቢ ፖሊሲ፡-** የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ ሌላኛው ዋና የመስኖ ልማት ፖሊሲው ደጋፊ ሲሆን አጠቃላይ ግቡም በተፈጥሯዊ፣ በሰው ሠራሽ እና ባህላዊ ሀብቶች እና አካባቢዎች ጤናማ አያያዝ እና አጠቃቀም አማካይነት የህይወት ጤናን ጥራት ማሻሻልና ዘላቂ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ማስፋፋት ነው፡፡
6. **የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ፣ ምርምር እና ልማት፡-** የአገሪቱን የብዝሃ ሕይወት አጠቃቀምን በተመለከተ ውጤታማ ጥበቃ፣ ምክንያታዊ ልማት እና ዘላቂ አጠቃቀም ላይ መመሪያ ይሰጣል ፣ እናም የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ እና ዘላቂ አጠቃቀምን በተመለከተ አጠቃላይ የፖሊሲ ደንቦችን ይሠጣል፡፡ በተለይም ከመስኖ መሰረተ

ልማት ግንባታ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የሆነ ለብዝሃ ሕይወት የሚሰጡትን ጥንቃቄዎችንና መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ያስቀምጣል፡፡

7. **የጤና ፖሊሲ፡-** የኢትዮጵያ የጤና ፖሊሲ የአገሪቱን የጤና ችግሮችንና ፍላጎቶችን በመለየት መፍትሄ በመስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በዚህም ረገድ ከመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ጋር ተያይዞ የሚከሰቱትን የተለያዩ የጤና ችግሮችን ለመቅረፍ ይረዳል፡፡
8. **የሴቶች ብሔራዊ ፖሊሲ፡-** ይህ ፖሊሲ የተቀረፀው በመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ተቋማት ውስጥ ፍትሃዊ እና ሥርዓተ-ጾታን ያገናዘቡ ተገቢው መዋቅርን ለመፍጠር ነው፡፡ ፖሊሲው በመስኖ ልማት ዘርፍ የሴቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥን ይደግፋል፡፡

### 4.3 የመስኖ ልማት ዘርፍ ዋና ተዋናዮች

በመስኖ ዘርፍ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ መስኖ ልማት ላይ በቀጥታ የሚሳተፉ ቁልፍ ተዋናዮች አሉ፡፡ እነዚህ ዋና ተዋናዮች በቅንጅት መስራታቸው ለዘርፉ እድገትና ውጤታማነት እና የመስኖን አለኝታ በአግባቡ ለመጠቀም ወሳኝ ነው፡፡

ሰንጠረዥ 6 የመስኖ ልማት ቁልፍ ተዋናዮች

| የመስኖ ልማት ቁልፍ ተዋናዮች | በመስኖ ስራ ያላቸው ድርሻ |
|---|---|
| የመስኖ ልማት ኮሚሽን | ከፍተኛ እና መካከለኛ መስኖ ልማት |
| ግብርና ሚኒስቴር | አነስተኛ መስኖ ልማት እና ኤክስቴንሽን |
| ክልሎች | ከፍተኛ፣መካከለኛ እና አነስተኛ መስኖ ልማት |
| ስኳር ኮርፖሬሽን | ከፍተኛ እና መካከለኛ መስኖ ልማት |
| የግል ባለሀብቶች | ከፍተኛ፣መካከለኛ እና አነስተኛ መስኖ ልማት |
| የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትና አርሶ አደሮች | መስኖ ልማት መጠቀምና ጥገና ማካሄድ |

## 4.4 በመስኖ ልማት የአገራት ልምድና ተሞክሮ

የተለያዩ አገራት የመስኖ ዘርፋቸውን ለማሳደግ የአጭርና ረጅም ጊዜ ስትራቴጅ ነድፈው በመንቀሳቀስ አዎንታዊ  እድገት አስመዝግበዋል፡፡ ለዚህም ለአብነት ከሚጠቀሱ አገራት መካከል እንደ ሞሮኮ፣ ግብፅ፤ ቱርክ እና ሲሪላንካ ይገኙበታል፡፡

ሞሮኮ በአለም ካሉ 25 ከፍተኛ የውሃ እጥረት ካለባቸው አገሮች መካከል አንዷ ናት፡፡ ላለፉት ሁለት አስርተ አመታት ይህንን የውሃ እጥረቷን ለመፍታት የሚያስችልና ያለውን ውስን የውሃ ሃብቷን በአግባቡ ለመጠቀም የሚረዳ እስከ እ.ኤ.አ 2022 ድረስ ስትራቴጅ በመንደፍ ካለው አጠቃላይ የቦይ መስኖ 50 ፐርሰንት የሚሆነውን በውሃ ቆጣቢ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች (የግፊት መስኖ ዘዴዎች) እንዲቀየሩ በማድረግ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ ማምጣት ችላለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአገራዊ የመስኖ ውሃ ቁጠባ ፕሮግራም በመቅረፅ ውሃ ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለማበረታታት ለመስኖ አልሚዎች መነሻ ኢንቨስትመንት ወጭን እስከ 60 በመቶ ድረስ በመንግስት እንዲሸፈን ከማድረጓም በላይ የውሃ ቁጠባን ለማሳደግ በውሃ አገልግሎት ክፍያ ላይና ለዘርፉ የሚውል የቴክኖሎጂ ኢንቨስትመንት ወጭን የማስመለስ ስራ ላይ ኢኮኖሚያዊ ማትጊያዎችን ተግባራዊ ማድረግ ችላለች፡፡ ከዚህ ሌላ የመንግስትና የግል አጋርነት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ውሃ ቆጣቢ የመስኖ አስተዳደር እንዲኖር ማድረግ ችላለች፡፡

በሌላ መልኩ ግብፅ በየጊዜው እያደገ የመጣውን የህዝብ ቁጥሯን የምግብ ፍላጎት ለማሟላትና የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ እንዲሁም የስራ እድል ለመፍጠር በየጊዜው የመስኖ ልማቷን እያስፋፋች ወደ 4 ሚሊዬን ሄክታር የሚጠጋ የመስኖ ልማት ማድረስ ችላለች፡፡ አብዛኛው የግብፅ የመስኖ ልማት አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አልሚዎች የተመሰረተ ሲሆን እስከ 62 በመቶ የሚሆነው ጠቅላላ ምርት የሚገኘው ከ 1 እስከ 3 ሄክታር ይዞታ ባላቸው በእነዚህ አልሚዎች ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተጠናከረ የግብርናና ተያያዥ ዕሴት ሰንሰለት ስርዓት በመፈጠሯ የመስኖ ዘርፉ በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ሚና መጫወት ችሏል፡፡ ለምሳሌ የመስኖ ልማትን ከአግሮ ኢንዱስትሪዎች ጋር ተሳስሮ እንዲሄድ በማድረግ የመስኖ ዘርፉ ብቻ 20 በመቶ ድረስ ጠቅላላ አገራዊ ገቢ ሲያበረክት ከግብርና ጋር የተሳሰሩት እነዚህ ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች ተያያዥ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉት የኢኮኖሚ ዘርፎች ደግሞ ሌላ ተጨማሪ 20 በመቶ አገራዊ ገቢ ማስገኘት ተችሏል፡፡ ከዚህ ሌላ የመስኖ ዘርፉ ብዙ የስራ እድል የፈጠረ ሲሆን በአጠቃላይ

በስራ ላይ ከተሰማራው ህዝብ በቀጥታና በተዘዋዋሪ 34 በመቶ የሚሆነውን ይዟል፡፡ በተለይም አገሪቷ ከሙያ ተቋምና ከዩኒቨርሲቲ የሚመረቁ 760 ሺህ ወጣቶች ውስጥ ብዙ ቁጥር ያላቸውን በመስኖ በማሰማራት ዘርፉን ያማዘመንና ለተማሩ ዜጎች የስራ ዕድል የመፍጠር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ማድረግ ችላለች፡፡

ሌላዋ በመስኖ ልማት ልትጠቀስ የምትችለው ቱርክ ስትሆን አገሪቱ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ወደ 3 ሚሊዬን ሄክታር የሚጠጋ የማህበረሰብ መስኖ ተቋማትን ገንብታለች፡፡ እነዚህን ተቋማት ከግንባታ ባለፈ የማስተዳደር ስራው መንግስትን ለከፍተኛ ወጭ በመዳረጉ ይህንን አቅጣጫ የሚቀይር ያልተማከለና አሳታፊ አስተዳደር ስርዓትን በመዘርጋት ለዘርፉ በመንግሰት የሚወጣውን የአስተዳደር እና ጥገና ወጭን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ችላለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአገሪቷ ከፍተኛ የውሃ እጥረት በመኖሩ ይህንን ዕጥረት ለመቅረፍ ውሀ ቆጣቢ የሆኑ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን አልሚዎች እንዲጠቀሙ የሚያበረታታ የገጠር ልማት ፕሮግራም በመቅረፅ የመስኖ ውሃ አጠቃቀምን ማሻሻል ችላለች፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በመስኖ ልማት ትኩረት አድርገው ከሚሰሩ አገራት የምትጠቀሰው ሲሪላንካ ነች፡፡ አገሪቱ ከኢትዮጵያ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ 80 ከመቶ ህዝቧ በገጠር የሚኖርና 90 ከመቶው ኑሮውን መሰረት ያደረገው ግብርና ላይ ነው፡፡ የመስኖ ልማት የግብርናውን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ድህነትን ለማስወገድ ረገድ የሚጫወተውን ሚና በመገንዘብ አገሪቱ ለዘርፉ ልዩ ትከረት በመስጠት ከሚታረሰው መሬት ሁለት ሶስተኛውን በመስኖ ለማልማት ችላለች፡፡ ሆኖም ግን የአገሪቱ የመስኖ ዘርፍ ከኢትዮጵያ ጋር እጅግ በተመሳሰለ ሁኔታ በዝቅተኛ ምርታማነት፣ የውሀ አቅርቦት እጥረት፣ ፍትሃዊ ያልሆነ የውሀ ስርጭትና ውጤታማ ያልሆነ የውሀ አጠቃቀም፣ ትርፋማ ያልሆነ የሰብል አመራረት ዘይቤ፣ በቂ ያልሆነ የመስኖ አውታሮች አስተዳደርና ጥገና፣ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ትኩረት አናሳ መሆን፣ የመስኖ አውታሮችን ማዘመን ያለመቻል፣ የቅንጅት ማነስ፣ የገበያ ትስስር ማነስና የግብርና ምርት ትርፋማ መሆን ያለመቻል፣ የመስኖ ተፋሰስ ጥበቃና ልማት ዝቅተኛ መሆን እና የመሳሰሉት በርካታ ችግሮች ነበሩበት፡፡ ሆኖም አገሪቱ የአስር ዓመት የመስኖ ልማት ስትራቴጂ ዕቅድ (እ.ኤ.አ. ከ 2006 — 2016) በመንደፍና ከላይ የተቀመጡትን የመስኖ ልማት ችግሮችን ዋነኛ የትኩረት ነጥቦች መሰረት ያደረገ ራዕይ ሰንቃ በመንቀሳቀስ እንዲሁም የመስኖውን ዘርፍ የአስተዳደር ሥርዓት ጭምር

በመቀየር (በአብዛኛው ተጠቃሚዎች ሃላፊነት እንዲወስዱ በማድረግ) በርካታ ጠቃሚ ለውጦችን ለማምጣት ችላለች፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት አገራት በመስኖ ልማት ዙሪያ ከሰሩት አንፃር ለአገራችን በተሞክሮ የሚከተሉትን መውሰድ ይቻላል፡፡

- የመስኖ ፖሊሲን ገምግሞ እና ክፍተቶችን ለይቶ ማሻሻል ብሎም በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ፤
- ውሃ ቆጣቢ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ማበረታታት፤
- በመስኖ ልማት የመንግስትና የግል አጋርነት ማጎልበት፤
- መስኖን በአግባቡ ለመጠቀም ጠንካራ የውሃ አስተዳደር መዘርጋት፤
- የውሃ ቁጠባን ለማሳደግ የውሃ አገልግሎት ክፍያ ስርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፤
- በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ የመጣውን የህዝብ ምግብ ፍላጎት ለማሟላትና የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የመስኖ ልማትን ማስፋፋት፤
- መስኖን በማስፋፋት ለተማሩ ወጣቶች የስራ እድል መፍጠር፤
- አነስተኛ ይዞታ ያላቸው የመስኖ አልሚዎችን ማበረታታት፤
- የተጠናከረ የግብርናና ተያያዥ ዕሴት ሰንሰለት ስርዓት በመፈጠር የመስኖ ዘርፉ በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወት ማድረግ፤
- የመስኖ ልማት ፈንድ እና የመስኖ ልማትን የሚቆጣጠር አሰራር ማጠናከር፤
- ያልተማከለና አሳታፊ የመስኖ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት፤
- የመስኖ ዘርፍን ከአግሮ ኢንዱስትሪዎች፣ የምርምር ማዕከላት፤ ዩኒቨርሲቲዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የአሰራር ቁርኝት ማዳበር፤
- የመስኖ ልማት ዋነኛ ችግሮችን ለመቅረፍ ትኩረት ያደረገ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፤

## 4.5 በዘርፉ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ከላይ በዝርዝር ከቀረቡት የአገራችን የመስኖ ልማቱ ያለበት ሁኔታ ትንተና እንዲሁም ጥልቅ በሆነ መልኩ ውስጣዊና ውጫዊ ጉዳዮች ላይ ከቀረበው ትንተና እንዲሁም የመስኖ ዘርፍ የስራ ድርሻ እና በመስኖ ልማት የተሻለ አፈፃፀም አሳይተዋል ተብሎ ከሚጠቀሱ

አገሮች ልምድና ተሞክሮ አንፃር የተገኙ አንኳር በዘርፉ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የአገሪቱ መስኖ ልማት ደረጃ ተፈላጊውን የምግብ፣ የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ እና የውጭ ገቢ ፍላጎቶች ጋር አለመመጣጠኑ፤
- ዘርፉ የሚፈለገውን ያህል የስራ እድል መፍጠር አለመቻሉ፤
- በመስኖ የግሉ ባለሃብት ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፤
- ለሴክተሩ የሚመደበው ፋይናንስ አነስተኛ መሆን፤
- በባለድርሻ አካላት መካከል የተቀናጀ አሰራርና አሳታፊነት ያለመኖር፤
- የመስኖ ልማት ላይ የሚሰሩ የመንግስት ተቋማት የስራ ድርሻ ድግግሞሽ መኖር፤
- የመስኖ ፕሮጀክቶች ምርታማነትና ዘለቄታዊነት ዝቅተኛ መሆን፤
- የመስኖ ተቋማት አስተዳደር ደካማ መሆን፤
- የመስኖ ፕሮጀክቶችን ለመምራት እና ለማስፈፀም የሚችል ብቃት ያለው ተቋምና የሰው ሃይል ያለመኖር፤
- የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ በታቀደላቸው ጊዜ፣ በጀትና በሚፈለገው ጥራት አለመጠናቀቃቸው፤
- የውሃ ቁጠባና የአየር ጠባይ ለውጥን ያገናዘበ የመስኖ አጠቃቀም ደረጃ ዝቅተኛ መሆን፤
- የመስኖ ልማቱ ከተዛማጅ የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር አለመቀናጀቱና በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ተሳስሮ አለመሄዱ፤
- የመስኖ የውሃ ክፍያ ስርዓት አለመዘርጋት፤
- በዘርፉ የተደራጀ መረጃ እና የመረጃ ስርዓት አለመኖር፤
- የመስኖ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን እንዲሁም አፈፃፀማቸውን ለመከታተል የሚያስችሉ ስታንዳርድ እና መመሪያ አለመኖራቸው፤
- በዘርፉ የሴቶችና የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፤

# 5. የትኩረት አቅጣጫ

## 5.1 ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች

የአገሪቱ የመስኖ ልማት ዘርፍ የሚከተሉት ራዕይ ተልዕኮና እሴቶች ይኖሩታል፡፡

**ራዕይ፡**

በ 2030 መስኖ የግብርናን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ሃብት የፈጠረ፣ የህዝቡን ኑሮ የቀየረ እና የኢኮኖሚ እድገት ያረጋገጠ የልማት ዘርፍ ሆኖ ማየት ነው፡፡

**ተልዕኮ፡**

የመስኖ አለኝታ በማጥናት የሚለሙ ቦታዎችን የመለየት፤ ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን በመስራት እና ግንባታ በማከናወን መስኖ እንዲስፋፋ የማድረግ እንዲሁም የመስኖ አውታሮች በዘለቄታዊነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማስተዳደርና የጥገና አገልግሎት ስራዎችን መስራት፤

**እሴቶች፡**

- ጥራት
- ፈጠራ
- ስነ-ምግባር
- አሳታፊነት
- አጋርነት
- ፍትሃዊነት
- ትጋትና ጥንካሬ
- ግልፀኝነት
- ሁልጊዜም መማር
- በጋራ መስራት

## 5.2 ስትራቴጅክ ምሰሶዎች፣ ግቦችና ቁልፍ ተግባራት

በመስኖ ዘርፍ የቀጣዩ አስር ዓመት የመሪ ዕቅድ ምሰሶዎች፣ ግቦችና ቁልፍ ተግባራት እንደሚከተለው ተለይተዋል፡፡ በተከታይነት በስትራቴጂክ ምሰሶዎች ስር ላሉ ግቦች መነሻ እና መድረሻ እንዲሁም ከግቦቹ የሚጠበቁ ውጤቶች ተቀምጠላቸው በሰንጠረዥ 7 በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

| ስትራቴጅክ ምሰሶ 1፡ በመስኖ ልማት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ |
| --- |
| ግብ 1.1. መካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮችን ጥናትና ዲዛይን ማሳደግ፤ |
